የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር 21
ሠመራ ጥር 7 ቀን2003 ዓ/ም

በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ምክር-ቤት ጠባቂነት የወጣ

8th year No.
SEMERA- 7thFebbruuar, 2003

ማውጫ

በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የስራ አመራር ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

..... ገጽ 1

አዋጅ ቁጥር 21/2003

በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የስራ አመራር ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ያለው የሰው ሃይል እትረት ደረጃ በደረጃ መቅረፍ፤ ለኢኮኖሚና ማህበራዊ መቀላጠፍ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ፤

በክልላዊ መንግስቱ በየደረጃው ተሰማርቶ ለሚገኘው የሰው ኃይል የሚሰጡ ስልጠናዎችን ራሱን የቻለ መንግስታዊ አካል መመስረት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፥-

የአፋር ብሄራ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ህገ-መንግስት አነቀጽ ንዑስ አአንቀጽ 3(ሐ) በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 1

አጭር ርዕስ፦

ይህ አዋጅ ‹‹ የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የስራ አመራር ኢንስቲቲዩት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 21/2003 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀጽ 2

ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ትርጉም የሚያሰጥ ካለልሆነ በስተቀር

1. ‹‹ክልል›› ማለት የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነው።
2. ‹›ኢንስቲተትዩት ›‹ ማለት የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ስራ አመራር ኢንስቲትዩት ነው።
3. ‹‹ማስተባበሪያ ቢሮ ›› ማለት የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት አቅም ግንባታ ማስተባበሪያ ቢሮ ነው።

ክፍል ሁለት

አንቀጽ 3

መቋቋምና አደረጃጀት

መቋቋም

1. የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ስራ አመራር ኢንስቲትዩት ከዚህ በኋላ ‹‹ኢንስቲትዩት›› እየተባለ የሚጠራ ህጋዊ ሰውነት ያለው ምንግስታ መስሪያ ቤት ሆኖ / በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ተጠሪነቱ ለማስተባበሪያ ቢሮ ይሆናል።

አንቀጽ 4

ድርጅታዊ መዋቅር እና ዋና ዋና ጽህፈት ቤት

1. ኢንስቲትዩቱ

   ሀ. ዋና ስራ አስኪያጅ፦

   ለ. ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞችና የስራ ክፍሎች ይኖሩታል።
2. ኢንስቲትዩት ጽህፈት ቤት በክልሉ ርዕሰ ከተማ ይሆናሉ።

አንቀጽ 5

አላማ

ኢንስቲትዩት የመንግስታቱን አካላት መንግስታዊ መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የስልጠና ፍላጎቶችን እያጠና የሙያ አቅም ግንባታ ስልጠና ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት በስልጠና አቅም በማጎልበት የክልሉን የልማት ጥረት ማገዝ ሲሆን እንዲሁም ከዚህ አኳያ የማማከር ዓላማ ይኖረዋል።

አንቀጽ 6

የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባር

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. የክልሉን መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶችን የስልጠና ፍላጎት ያጠናል።ከስራ አመራር ተግባር ጋር የተያያዙ ሌሎች ጥናቶችንና ምርምሮች ያካሂዳል።
2. የተጠና የስልጠና ፍላጎት ላይ ተመስርቶ በየሴክተሩ ለሚገኙ ሰራተኞች የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠና ይሰጣል፤ያማክራል።
3. የክልሉ የመንግስት ሰራተኞች የተሰጣቸውን ስራ በብቃት እንዲወጡ አስፈላጊውን የስራ አመራር ስልጠና ይሰጣል።
4. ‹‹ሥልጠና ››ላጠናቀቁ ሰልጣኞች የምስክር ወረቀት ይሰጣል።
5. ከተለያዩ የክልሉ መንግስት አካላትና መንግስታ ምስሪያ ቤተቶች፤እንዲሁም መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚቀርቡለትን የስልጠና ደረጃ መዝኖ ይወስናል ። ከሚመለከተው አካል ወይም መንግስታ መስሪያ ቤት ወይም ምንግስታዊ ካለሆኑ ድርጅት ጋር በመተባበርም ስልጠና ላጠናቀቁ ሠልጣኞች የምስክር ወረቀት ይሰጣል።
6. የባለሙያዎችን ድጋፍ ለማግኘት ይረዳ ዘንድ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋሞች ጋር የስራ ግንኙነት ያደርጋል።
7. አግባብ ካለው አካል ጋር ውል ይዋዋላል።
8. ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ስራዎችን ያከናውናል ።
9. ከስራ አመራር ጋር የተያያዙ ጥናቶችን ያካሂዳል፤የምክር አገልግሎትም ይሰጣል።
10. የንብረት ባለቤት ይሆናል ይከሰሳል፤
11. ለሚሰጠው አገልግሎት ተመጣጣኝ ክፍያ ሊሰበሰብ ይችላል።
12. ለስራ አመራር ስልጠና የጥናት ፕሮጀክት በማዘጋጀት ከተለያዩ ምንጮች ገንዘብ የሚያገኝበትን ሁኔታ ይፈጥራል።

አንቀጽ 7

የዋና ስራ አስኪያጅ ተጠሪነት

ዋና ስራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለማስተባበሪያ ቢሮ ይሆናል።

አንቀጽ- 8

የዋና ስራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባር

1. ዋና ስራ አስኪያጁ በዚህ አዋጅ አንቀጽ(6) ለኢንስቲትዩቱ የተ ሰጠውን ስልጣንና ተግባር ከሚያከናውናቸው በተጨማሪ፡-

ሀ. በሲቪል ሰርቪስ ህግ መሰረት ለኢንስቲቱዩቱ የሚያስፈልጉትን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ይቀጥራል፤ያስተዳድራል፤ያሰናብታል። በቋሚነት ሊቀጥራቸው የማይችላቸውን ባለሙያዎች በኮንትራት ይቀጥራል፤ያስተዳድራል ኮንትራታቸውን ያርጣል።

ለ. ኢንስቲቱዩትን ስራዎች ይመራል ያስተዳድራል ይቆጣጠራል።

ሐ. የኢንስቲቱዩትና የአጭርና ረጅም ጊዜ ዕቅድ እንዲሁም ዓመታዊ የስራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለማስተባበሪያ ቢሮ ያቀርባል ሲፈቀድለትም ስራ ላይ ያውላል።

መ. ለኢንስቲቱዩቱ በተፈቀደልት የስራ ፕሮግራምና በጀት መሰረት ገንዘብ ወጪ እንዲሆን ያደርጋል ስራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል።

ሠ. ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረግ ግንኙነት ሁሉ ተቋሙን ይወክላል።

ረ. የኢንስቲቱዩቱን የሩብ ዓመትና ዓመት የስራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለማስተባበሪያ ቢሮ ያቀርባል።

ሰ. የኢንስቲትዩቱ /ገንዘብና ንብረት በአግባቡ መያዙን ያጋግጣል።

ሸ. ከማስተባበሪያ ቢሮ የሚመደቡለትን ሌሎች ስራዎች ያከናውናል።

2. ከማስተባበሪያ ቢሮ እያሳወቀ ኃላፊነቱ በብቃት ለማውጣት በሚያስችለው መልኩ ከስልጠና ተግባሩ በመቀነስ ለበታች ኃላፊዎች ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

ክፍል ሶስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ- 9.

በጀት

የኢንስቲቱዩት በጀት ምንጭ

1. በክልሉ መንግስት በሚመደብ በጀት
2. ከዕርዳታና ከሌሎች ምንጮች የሚገኝ ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረት ሊሆን ይችላል።

አንቀጽ -10

የሂሳብ መዛግብት አያያዝ

1. ኢንስቲቱዩት የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የኢንስቲቱዩት የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ወይም እርሱ በሚወክለው ኦዲተር በየአመቱ ይመረምራል።

አንቀጽ-11

የተሻሩ ህጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ በዚህ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዩች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

አንቀጽ- 12

ደንብን የማውጣት ስልጣን

የክልልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ተከትሎ ደንብ የማውጣት ስልጣን ይኖረዋል።

አንቀጽ-13

አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።።

ሰመራ ጥር 7 ቀን 2003 ዓ.ም

ኢስማኤል አሊ ሴሮ

የአፋር ብ/ክ/መንግስት ርዕሰ መስተዳድር